ስር ነቀል የስርዓተ-ፆታ ለውጥ
አምጭ ስልቶችን በመተግበር
የሴቶችን የመሬትና ተያያዥ
ሃብት ባለቤትነት መብት
ማረጋገጥ

IFAD
Investing in rural people



# በኢትዮጵያ የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለማጠናከር ስር ነቀል የስርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን መተግበር

## መሠረታዊ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና




የጥናት ማጠቃለያ አጭር መግለጫ

CIFOR · World Agroforestry · Alliance Bioversity & CIAT · INTERNATIONAL FOOD POLICY RESEARCH INSTITUTE (IFPRI) · ግብርና ሚኒስቴር MINISTRY OF AGRICULTURE

© እ.ኤ.አ 2024 በአለም አቀፍ የደን ምርምር እና የአለም ጥምር ግብርና (CIFOR-ICRAF) እና አለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD)

ሰቲብኒያቲ አትማጃ (በአለም አቀፍ የደን ምርምር እና የአለም ጥምር ግብርና (CIFOR-ICRAF) እ.ኤ.አ 2024. በኢትዮጵያ የሴቶችን የመሬትና ተያያዥ ሃብት ባለቤትነት መብቶች ለማጠናከር ሰር ነቀል የሰርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን መተግበር አስፈላጊነት፤ መሰረታዊ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና። ሰር ነቀል የሰርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን በመተግበር የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት ሃብት መብት ማረጋገጥ። በአለም አቀፍ የደን ምርምር እና የአለም አቀፍ ጥምር ግብርና (CIFOR-ICRAF) ቦጎር፥ ኢንዶኔዥያ።

**ሙያዊ ቅንብር፥ እርትኦት፥ ቅርጽና አቀማመጥ፡ ካነድስ ኮሌክቲቭ** KANDS Collective | hello@kandscollective.com

**የላይኛው ሽፋን ምስል:** በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የተሳትፏዊ አነስተኛ መሰኖ ልማት ፕሮግራም II ባልሆነ መንደር የCIFOR ተመራማሪ፣ የቀበሌ ልማት ሰራተኞች እና የሀገር ሽማግሌዎች በጋራ በመሆን የጥናት ቡድኑ ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ስለ ሰርዓተ-ፆታ ደንቦችና ልማዶች ለመረዳት የአትኩሮት ቡድን ውይይት ካደረገ በኋላ በአካባቢው ሽማግሌዎች በጸሎት የተመራ የጥናት ቡድኑን ሲመርቁ እ. ኤ. አ 2023, ሰቲብኒያቲ  አትማጃዶ/ር።© 2023

**የታችኛው ሽፋን ምስል፡-** በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሰት የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና ልማዶችን ለመረዳት የምርምር ቡድን፣ የቀበሌ ልማትሠራተኞች እና ሴት የሰርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ተሳታፊዎች የአትኩሮት ቡድን ውይይት ካጠናቀቁ በኋላ አብረው የተነሱት ፎቶ ነው። ከጀርባ ያለው ባነር የቤቱ ባለቤት የሆኑት ጥንዶች ከሰርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰቦች ስልጠና በመመረቃቸውንና እንኳን ደስ አላችሁ የሚል መልዕክት ይዟል። © 2023, በርሳቤህ ኃይሉ

**ለፕሮጀክቱ የተዘጋጀ፤** ሰር ነቀል የሰርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን በመተግበር የሴቶችን የመሬትና ተያያዥ ሃብት ባለቤትነት መብት ለማረጋገጥ የሚደረገው ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ የሚመራው በአለም አቀፍ የደን ምርምር ማዕከል (CIFOR)፤ በአለም ጥምር ግብርና (ICRAF)፤ ከዓለም አቀፍ ብዙሃ ህይወት ጥምረት (Alliance of Bioversity International) እና ሲአይኤቲ (CIAT)  ከዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት (IFPRI) እና በአለም አቀፉ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) ድጋፍ ነው።

**በግብርና ሚኒስቴር የፕሮግራሙ ተጠሪ:**

ግብርና ሚኒስቴር MINISTRY OF AGRICULTURE

ኑረዲን አሳሮ
ብሔራዊ ፕሮግራም አስተባባሪ
የተሳትፏዊ አነስተኛ መሰኖ ልማት ፕሮግራም II
ግብርና ሚኒስቴር
nuredin.asaro@moa.gov.et

## ስለ ፕሮግራሙ አጀማመር

### የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለማጠናከር ሰር ነቀል የሰርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን መተግበር

እ.ኤ.አ 2020 የዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) ከየዓለም አቀፍ የደን ምርምር እና የዓለም ጥምር ግብርና (CIFOR-ICRAF)፣ የአለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት (IFPRI) እና የብዝሃ ሕይወት ዓለም አቀፍ ጥምረት እና የዓለም አቀፍ የትሮፒካል ግብርና ማዕከል (CIAT) በጋራ ለመስራት በመስማማት በተመረጡት የIFAD ፕሮጀክቶች ላይ ሰር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን (GTAs)  ከገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስልቶች ጋር በማዋሀድ የሴቶችን የመሬትና ተያያዥ መብት ባለቤትነት ለማስገንዘብ እና ለማጎልበት ሰርቷል።

https://www.cifor-icraf.org/wlr
https://www.ifad.org/en/gender_transformative_approaches

## የፕሮግራሙ ተጠሪዎች

CIFOR World Agroforestry

**አን ኤም. ላርሰን፣**
**የአስተዳደር፣ ፍትህ እና ደህንነት ቡድን መሪ**
a.larson@cifor-icraf.org

Alliance Bioversity & CIAT

**ማርሌን ኤልያስ፣**
**የሰርዓተ ፆታ ማካተት ዳይሬክተር**
marlene.elias@cgiar.org

IFAD Investing in rural people

**ቲሽሪንግ ቾደን፡**
**በሥርዓተ-ፆታ ቡድን**
**የሥርዓተ-ፆታ እና ማህበራዊ ማካተት ቴክኒካል ባለሙያ**
t.choden@ifad.org

**ሪኬ ግራንድ ኦሊቬራ፡**
**የመሬት ሰሪት ቡድን መሪ**
**የቴክኒክ  ባለሙያ**
r.olivera@ifad.org

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) የገንዘብ ድጋፍ ነው። በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት ግኝቶች፣ አስተያየቶች፣ ትርጓሜዎች እና መደምደሚያዎች የጸሐፊዎቹ እንጂ የግድ የኢፋድን፣ የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ፣ የአባላቱን ወይም የሚወክሉትን አባል ሀገራትን አመለካከት የሚያንፀባርቁ አይደሉም። አለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ በዚህ ሥራ ውስጥ የተካተቱትን መረጃዎች ትክክለኛነት አያረጋግጥም። በዚህ ስራ ውስጥ በማንኛው ካርታ ላይ የሚታዩት ድንበሮች፣ ቀለሞች፣ ስያሜዎች እና ሌሎች መረጃዎን ሕጋዊነት ወይም እንደዚህ ያሉ ድንበሮችን ማጽደቅና ተቀባይነት መስጠት የሚያሳዩ ምንም ዓይነት ውሳኔ ዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድን አይመለከትም።



# የጽሑፉ ይዘት

የኢፋድ ፕሮጀክት 2

ኢትዮጵያ 4

የሥርዓተ ፆታ ትንተና ዘዴዎች 6

ከኢትዮጵያ ምን እንማር 7

ቁልፍ ትምህርቶች/ልምዶች 9

ዋቢ ምንጮች 11

ምክረ ሃሳቦች 12

# IFAD ፕሮጀክት አውታረ መረብ



ኮሎምቢያ
የገጠር ሰራ ፈጠራ
አቅም ግንባታ
ፕሮግራም
(2012- 2022)

ጋምቢያ
የአነስተኛ ይዞታ ግብርና
ሽግግር ፕሮግራም
ድርጅቶች ማጠናከሪያ
(ROOTS)
(2019 - 2026)

ኒጀር*

ዩጋንዳ
ብሔራዊ የፓልም ዘይት
ፕሮጀክት (NOPP)
(2019- 2029)

ኢትዮጵያ
ተሳትፏዊ አነስተኛ
መሰኖ ልማት
ፕሮግራም ፪
(PASIDP-II)
(2017-2024)

ክይርጋዝስታን
የገበያ ተደራሽነት
ፕሮጀክት(2018 -
2023)

ባንግላዲሽ
ቻር ልማትና የሰፈራ
ፕሮጀክት IV (CDSP
IV) (2011 – 2022)

# መግቢያ

ይህ ተከታታይ አጭር መግለጫ በሰድስት አገሮች (ኪርጊሰታን፣ ዩጋንዳ፣ ጋምቢያ፣ ኢትዮጵያ፣ ባንግላዲሽ እና ኮሎምቢያ) ውስጥ በተካሄዱጅ የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔዎች የተገኙ ቁልፍ ትምህርቶችን ያጠቃልላል። የዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ስር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን የመተግበር ሂደት ውስጥ ይህ አጭር መግለጫ በጋራ መማማርን፣ የእውቀት ልውውጥን እና የአቅም ግንባታን፣ መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋትና እንዲሁም በጥናት የተረጋገጡ ግኝቶችን በህግ፥ በደንብና እና በፖሊሲ ማዘጋጀት ሂደቶች ውስጥ እንዲካተቱ ያማመቻቸት ሚና ይኖረውል።

## ዳራ

የተባበሩት መንግስታት አጀንዳ 2030ን ለማሳካት የሰርዓተ-ፆታን እና ሌሎች የማህበራዊ እኩልነት ክፍተቶችን ለመቀነስ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን መከተል እንድሚያስፈልግ ስምምነት ላይ ተደርሷል። የመሬትና ተያያዥ ሃብት የማፍራት፤ የአጠቃቀምና የመወሰን መብቶች እድሎ የሚበዛብት አንዱ መስክ ነው። በልማት ተግባራት እና ፖሊሲዎች ውስጥ፣ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን እና የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለመደገፍ የተሰሩት ሰራዎች መሰረታዊ ችግሮቹን የዳሰሱ ባለመሆናቸው የሚፈለገውን ውጤት አላመጡም። ስር ነቀል የሥርዓተ ፆታ ለውጥ አምጭ ስልቶችን ከመሬት እና ተያያዥ የሃብት ባለቤትነት መብት ፖሊሲዎች፤ ልማዶች፡ አሰራሮች ጋር በማጣመርና በማዋሀድ መተግበር ውጤታማ ሊያደርግ ይችላል።

የመሬት አቅርቦትንና ሃብትን መቆጣጠር እንዲሁም በሀብቶቹ ላይ መወሰን ሴቶችን ለማብቃት ወሳኝ ሚና አላቸው። ይሁን እንጂ ሴቶች በቂ ያልሆኑ የህግ ማዕቀፎች፣ የፖሊሲ አተገባበር ክፍተት እና የተዛቡ ልማዳዊ አመለካከቶች የመሳሰሉ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል። እነዚህም መሬትን እና ተያያዥ ሀብቶችን የማግኘት፣ የመጠቀም እና የመቆጣጠር እድላቸውን ገድቦታል። በግብርናው ዘርፍ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችና የልማት ውጥኖች እውቅና ካልተሰጣቸው ኢ-ፍትሃዊነትን ከማጠናከር አልፎ የተዛባ እኩልነትን ሊያባብሱ ይችላሉ። ስለዚህ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን፤ የሴቶችን መብት ለማስከበር፤ የመሬት ተጠቃሚነትንና ባለቤትነት መብታቸውን ለማረጋገጥ ተቋማዊ የአሰራር ችግሮችን መፍታት አስፈላጊ ነው።

ስር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን መተግበር ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እንቅፋት የሆኑ መሰረታዊ ምክንያቶችን ለምሳሌ ውሳኔ አሰጣጥ እና በሀብት ቁጥጥር ላይ ሴቶች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስችላል። ስልቶቹም ዘላቂ እና ሰፊ ለውጦችን በማበረታታት፣ ለሴቶች ማብቃት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ያለሙ ናቸው። ስር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን (GTAs) በገጠር ልማት ፕሮግራሞች እና ተግባራት ውስጥ ማካተት ለሴቶች መሬት ባለቤትነት መብቶቸን በማጎናጸፍ በገጠር መሰረተ ልማት አገልግሎቶች እና በገበያ ትሥሥር ላይ ያሉ እድሎዎችን ለመፍታት ያስችላል። ይህም የሴቶችን ህይወት በማሻሻል እና ለመብቶቻቸው እውቅና ጥበቃ በመስጠት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያስችላል። የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለማሳለጥ መሬት ላይ ያሉ የሥርዓተ ፆታ ተለዋዋጭነቶችን መረዳትን ይጠይቃል። እንዲሁም አድሎአዊ የሥርዓተ ፆታ ግንኙነቶችን የሚያጠናክሩ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ለመለወጥና አስቻይ ነጥቦችን ለመለየት ሰፊ ፕሮግራማዊ ንድፍ እና አተገባበር ስልቶችን በጥልቀት ማሰብንም ጭምር ይጠይቃል።

## ዓለም አቀፍ የትኩረት አቅጣጫዎች

የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብቶችን እውቅናን ለመስጠት እና የህግ ከለላን ለማጠናከር፣ ዓለም አቀፉ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) ለሦስት ዓመታት የሚቆይ ፕሮጀክት (2021-2024 እ. ኤ. አ) ስር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን መተግበር (GTAs) በዓለም አቀፍ ደረጃ ጀምሯል።

ፕሮጀክቶቹም የሚተገበሩባቸው ሰድስት አገሮች፡- ባንግላዴሽ፣ ኮሎምቢያ፣ ኢትዮጵያ፣ ኪርጊዝስታን፣ ጋምቢያ እና በዩጋንዳ ውስጥ ሲሆን ከዓለም አቀፉ የደን ምርምር ማዕከል እና ከዓለም አቀፍ ጥምር ግብርና ማዕከል (CIFOR-ICRAF)፣ ከዓለም አቀፉ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ተቋም (IFPRI) እና ከባዮቨርሲቲ ኢንተርናሽናል እና ዓለም አቀፍ የሞቃታማ/ትሮፒካል ግብርና ማዕከል (CIAT) ጋር በመተባበር ተግባራዊ አድርጓል። ይህ ፕሮጀክት እውቀትን በማጋራት እንዲሁም ፖሊሲዎችን፣ አሰራሮችን እና ልምዶችን በማሻሻል ስር ነቀል የሥርዓተ-ፆታ ለውጥ አምጪ ስልቶችን (GTAs) ለማስፋፋት ያለመ ነው።

የፕሮጀክት ትግበራ ቡድኑ በእያንዳንዱ አገር ከኢፋድ ፕሮጀክት ሰራተኞች ጋር በመተባበር፣ ከሚደረጉ ጥረቶች ለመማር፣ እሴት ለመጨመር እና ለማጋራት ክፍተኛ ጥረት አድርጓል። የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለማጠናከርና ለማስፋፋት ተገቢ እና አግባብነት ያላቸው አካሄዶች ተለይተዋል። እያንዳንዳቸው የIFAD ፕሮጀክቶች አንዱ ከሌላው የተለየ ሲሆን፣ የተለየዩ የፕሮጀክት አተገባበር ደረጃዎችን እና የጊዜ ሰሌዳዎች ያሏቸው እና እንዲሁም የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሰርዓተ ጾታ ነክ ጉዳዮችን፤ ከመሬት ባለቤትነት መብትና ሀብቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለመፍታት ያለሙ ናቸው። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ጥቂቶቹ ብቻ በግልጽ በመሬት እና ተያያዥ የሀብት ባለቤትነት መብቶችና በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ ትኩረት አድርገዋል። በተለያዩ ፕሮጀክቶች እና አውዶች ውስጥ ትምህርቶችን ለመሰብሰብ እና መልካም ልምዶችን/ትምህርትን ይሰራል። ይህ የፕሮጀክቱ ተነሳሽነት ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ተግበራ እና አውዶች የተገኙ በጎ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ለመሰብሰብ፥ ለማስፋፋት እና መማርን ለማበረታታት ይሰራል። የተገኙት በጎ ልምዶች/ትምህርቶች ከ30 በላይ በIFAD ከሚደገፉ ፕሮጀክቶች እና ከዚያም በላይ ካሉት አካላት ጋር ይጋራሉ።



# የሥርዓተ ፆታ ትንተና

ይህ ተከታታይ አጭር መግለጫ ከሰድስት አገሮች ውስጥ በተካሄዱ የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔዎች የተገኙ ቁልፍ ትምህርቶችን ያጠቃልላል። ይህ አጭር መግለጫ በጋራ መማማርን፣ የእውቀት ልውውጥን እና የአቅም ግንባታን፣ መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋትና እንዲሁም በጥናት የተረጋገጡ ግኝቶችን በህግ፥ በደንብና እና በፖሊሲ ማዘጋጀት ሂደቶች ውስጥ እንዲካተቱ ያመቻቻል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጀንዳ 2030ን ለማሳካት እና በመሬት መብቶች ላይ የሰርዓተ-ፆታ ኢ-ፍትሃዊነትን ለመቀነስ ስር ነቀል የሰርዓተ-ፆታ ሽግግር ዘዴዎችን (GTAs) ከልማት አጀንዳዎች ጋር ማቀናጀት ወሳኝ ነው። የሥርዓተ-ፆታ ኢ-ፍትሃዊነትን መንስኤዎችን በውሳኔ አሰጣጥ እና በንብረት ቁጥጥር ላይ ዘላቂ ለውጦችን በማጎልበት፣ የሴቶችን የመሬትና ተያያዥ ሀብትን ለመጠቀም እና ለማስተዳደር ሰልታዊ ማዕቀፍ በማቅረብ አድሎአዊ ልማዶችን፤ አመለካከቶችን እና ተቋማዊ እንቅፋቶችን ይገዳደራሉ። ፕሮጀክቱ እውቀትን በማካፈል እና ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን እና ልምዶችን በማሻሻል የበለጠ ተጽዕኖ ለመፈጠር ያለመ ነው። ስለሆነም በአካባቢያዊ ሁኔታ፣ በሥርዓተ-ፆታ ተለዋዋጭነት እና በመሬት መብቶች መካከል ያለውን ውስብስብ ግንኙነት ለመፈተሽ በሰድስቱም አገሮች ጥልቅ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ተካሄዷል።

በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና በአዳዲስ ፈጠራዎች ላይ የተመሠረተው ይህ ስልት (GTA)፣ ሴቶች መሬት የማግኘት ዕድላቸውን የሚወስኑ ሁኔታዎችን፣ የሕግ ማእቀፎች፤ ተሞክሮዎች እና በእውቅና እና በትግበራ መካከል ያሉ ክፍተቶችን አጥንቷል። የማህበረሰብ ገጽታዎችን ለመረዳት ከፕሮጀክት ሠራተኞች ጋር ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ቃለ መጠይቆችን በመጠቀም እና በሰርዓተ-ፆታ የተለያዩ የአትኩሮት ቡድን ውይይቶችን (FGDs) እንዲሁም የጥንድ፣ የቤተሰብ እና የጓደኛ ቃለ መጠይቆችን (CFFI) የመሳሰሉ የተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ትንተናው በሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብት እና ተያይዥ ሀብት ላይ ያሉ የሥርዓተ-ፆታ ኢ-ፍታዊነት መሠረታዊ መንስኤዎችን ሁለንተናዊ ግንዛቤ ለመስጠት እና በቤተሰብ ደረጃ GTA ሊኖረው የሚችለውን ተጽዕኖ ገምግሟል። ይህም የIFAD ፕሮጀክት ንድፍ እና አፈጻጸምን በተለያዩ አውዶች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና ሴቶችን የማብቃት ሂደት መረጃ ይሰጣል።

ስለ ሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴ የበለጠ ዝርዝርመረጃ ለማግኘት እባክዎን የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴ ሪፖርትን ይመልከቱ።



ስለ ሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴ የበለጠ ዝርዝርመረጃ ለማግኘት እባክዎን የሥርዓተ-ፆታ **ትንተና ዘዴ ሪፖርትን ይመልከቱ።**

# የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴዎች

ይህ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዘዴ ዓይነታዊና የአንድ ጉዳይ ጥናቶችን ከGENNOVATE እና Pro-WEAI የተወሰዱ ፕሮቶኮሎችን ተጠቅሟል። በኢትዮጵያ የሚከተሉት የተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡



**ቁልፍ መረጃ ሰጪ ግለሰቦች ጋር ቃለ-መጠይቆች (KII):**
ከፕሮጀክቱ ሠራተኞች ጋር

- መግቢያ እና ፕሮጀክቱ ሰርዓተ-ፆታን እንዴት እንደሚመለከተው።
- በሴቶች የመሬት መብቶች ላይ ያሉትን መሰናክሎች እና ተልምዶአዊ ገደቦችን መለየት።
- ነባር እና ሊተገበሩ የሚችሉ ተግባራትን፣ መልካም ተሞክሮዎችን፣ አደጋዎችን እና ውድቀቶችን መመርመር።



**የአትኩሮት ቡድን ውይይቶች (FGD) ከሥርዓተ**
ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ተሳታፊዎች እና ተሳታፊ ካልሆኑት ጋር

- የማህበረሰቡን ሁኔታ እንዴት እንደሚረዱ፡ በአትኩሮት ቡድን ተሳታፊዎች  እይታ የማህበረሰቡን ሁኔታ መግለጽ።
- ነባር መብቶች፡ ተሳታፊዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የንብረት ባለቢትነት መብቶችን እና ከመብቶቹ ጋር የተያያዙ ደንቦችን እንዴት እንደሚያሳድጉ ግንዛቤን ማሳደግ።
- መብቶችን የሚያደናቅፉ ተግዳሮቶች እና እንቅፋቶች፡ የአካባቢ መብቶች (መደበኛ እና ልማዳዊ) በመረዳት የደህንነት እና የሰላመና የመረጋጋት ሁኔታዎችንና ምክንያቶችን መለየት።
- ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎች እና የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተጽዕኖ፡ ተሳታፊዎች በሀብት ባለቤትንት መብቶች እኩልነት ላይ ያተኮሩ እርምጃዎች እና የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ሊያሳድር ከሚችለው ተጽዕኖ ጋር በተያያዘ ያላቸውን አመለካከት መረዳት።
- የምግብ አይነቶች ብዝሃነት፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ ባለፉት 24 ሰዓታት ውስጥ የተመገበውን የምግብ አይነት ሰብጥር መዘርዘር



**የማህበረሰብ ገጽታዎችን ለመለየት ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን በቡድን እና በግለሰብ ደረጃ ማነጋገር**

- ስለማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ግብርና ነክ እና ፖለቲካዊ መረጃዎችን መሰጠት፣ እንዲሁም ቁልፍ ሀብቶችን በተመለከተ የተደራሽነት፣ የአጠቃቀም እና የቁጥጥር ወቅታዊ ሁኔታዎችን መግለጽ
- በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ የሥርዓተ ፆታ ወጎችን/ልማዶችን መንሰሄዎች መረዳት አስፈላጊ ነው፣ እነዚህ መንሰሄዎች ሴቶች የሀብት መብቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ አውቅና እንዲያገኙና እንዳይጠቀሙባቸው የሚያደርጉ ወይም የሚያስገድዱ ናቸው።



**ጥንዶች፣ ቤተሰብ እና ጓደኞች ከተጋቡ ጥንዶች እና ከተመረጡ ቤተሰብ/ጓደኛ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ**

- ለማምረቻነት የሚያስፈልጉ ሀብቶች ተደራሽነትና እና ቁጥጥርን በተመለከተ
- የሥራ ክፍፍል እና ሃላፊነቶችን በተመለከተ
- የገቢ ምንጭን በተመለከተ፡ የቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሰጣጥ እና በማህበረሰብ አደረጃጀቶች ላይ ተሳትፎ ማድረግ
- የአሁን ያሉበትን ሁኔታ ከቀድሞው ጋር ጠቃላይ ደህንነትን እና በሰርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን በተመለከተ ወይም የሀብት ባለቤትነት  መብቶችን ሙሉ በሙሉ እውቅና አለመሰጠትና መጠቀምን የሚገታ የሰርዓተ-ፆታ ልማዳዊ አስተሳሰብን መታገል።



# ከኢትዮጵያ ምን እንማር?

## የፕሮጀክቱ አውድ

በኢትዮጵያ ውስጥ የዓለም አቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ ሃገራዊ ፕሮግራም ሁለት ዋና ዋና አላማዎች አሉት። በተሻለ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ በተለይም በውሃ አያያዝ፣ የስነ-ምህዳር እና የኑሮ ዘዴዎች ምርታማነት እና ተጋላጭነትን ማሻሻል፤ እንዲሁም ለገበያ፣ ለፋይናንስ፣ እና ለግብርና ቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ማሳደግና ከግል ዘርፍ ጋር ትስስር መፍጠር ነው። የሚያካትታቸው ዋና ዋና የኢንቨስትመንት መስኮች፡- አነስተኛ የመስኖ ልማት፣ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር፣ ገጠር ተኮር ፋይናንስ አካታችነት፣ ማህበረሰብ ተኮር የአርብቶ አደር ቡድኖች ልማት እና የዕውቀት ልውውጥ እንዲሁም ከግሉ ሴክተር፣ ከምርምር ተቋማት እና ከሌሎች ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ጋር መተባበር ይገኙበታል። መርሃ ግብሩ ቀጣይነት ያለው ግብርናን ማስተዋወቅ፣ የገጠር ኑሮን ማሻሻል እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን ታሳቢ ያደረገ ነው።

በኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ ፕሮጀክት/ኢኒሸቲቭ የተመረጠው ፕሮግራም የተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ሁለትኛ ፕሮግራም ነው። ከ2009 እስከ 2016 ዓ.ም. በሚተገበረው ተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ሁለተኛ ፕሮግራም፣ በአራት ክልሎች 18,400 ሄክታር የሚሸፍኑ የአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማልማት እና 108,750 ድሃ የገጠር ቤተሰቦችን ተጠቃሚ ለማድረግ ግብ በመያዝ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ፕሮግራሙ ለሴቶች፣ ለወጣቶች፣ እና ለተጋላጭ የህብረትሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል። የግብርና ምርትና ምርታማነትን እና የስነ-ምህዳር ተጋላጭነትን ከማሻሻል በተጨማሪ፣ ፕሮግራሙ 15,000 አዳዲስ የስራ እድሎችን በመፍጠር ከፍተኛ ገቢ እና የማህበረሰብን ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭነትን መቀነስን እንደሚያስችል ይጠበቃል። በተጨማሪም ፕሮግራሙ አነስተኛ አርሶ አደሮች ምርታማነታቸውን፣ ተወዳዳሪነታቸውን፣ እና ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ ከገበያዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይደግፋል። በውጫዊ ችግሮች እና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከሚመጡ ችግሮች የመቋቋም አቅማቸውን ለማሳደግ አልሞ ይሰራል።

በዚህም መሰረት፣ ፕሮግራሙ የአርሶ አደሮችን ብልጽግና፣ የምግብ ዋስትና እና የአመጋገብ ሁኔታ ለማሻሻል ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም የፕሮጀክቱ ተሳታፊዎች የልማት ሂደቱን እንዲመሩ ያሰለጥናል እንዲሁም ሴቶች በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ሌሎች አደረጃጀቶች የውሳኔ ሰጪነት ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ ያበረታታል።

ከተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም II የተገኘው ልምድ የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ የተባለውን ሰር ነቀል የሥርዓተ ፆታ ለውጥ አምጭ ስልት መተግበሩ አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ የአቅም ግንባታ ዘዴ በመጀመሪያ በጋና ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ የግብርና ሚኒስቴር በአነስተኛ እና ጥቃቅን መስኖ ድጋፍ (SMIS) በተባለ ቀድም ሲል ከነበረ ፕሮጀክት ተቀባይነት አግኝቷል። በኢትዮጵያ ይህ ዘዴ ያገቡ ጥንዶችን ኢላማ ያደረገ፣ እንዲሁም የስራ ጫና እና በቤተሰብ አባላት ደራጅ የውሳኔ ሰጭነት የሃይል አለመመጣጠንን ለመለየት፣ ችግሩን ለመገንዘብና ለመፍታት ይቻል ዘንድ ቃል ለመግባት ለመተግበር የጋራ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ። እያንዳንዱ የሥርዓተ ፆታ አርአያ ቤተሰብ እራሱን ከለወጠ በኋላ ቢያንስ ሶስት ቤተሰቦችን እንዲመለምል ይጠበቃል፣ እነዚህም በተራቸው አዳዲስ ቤተሰቦችን እንዲመለምሉ ታሳቢ ያደርጋል።

የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ (GMF) በተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም II በ2011 ዓ.ም. በሶስት አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ በሶስት መንደሮች 44 አርአያ ቤተሰቦችን በማካተት በሙከራ ደረጃ ተጀምሮ ነበር። ስለሆነም የተገኙት ውጤቶች በጣም አበረታቾች ነበሩ። ፕሮጀክቱ ተሞክሮውን በተጨማሪ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለማስፋፋት በመወሰን አሁን በ56 የአነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ 744 አርአያ እና 3,157 ተከታይ ቤተሰቦችን፣ ጠቅላላ 3901 ቤተሰቦችን በማካተት እየተተገበረ ይገኛል።



በኦሮሚያ ክልል ከሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ (መጋቢት 2015፣ © 2023, ተሾመ በየነ)።

## የሥርዓተ-ፆታ ትንተና

ለሥርዓተ ፆታ ትንተና ስራው የተዘጋጁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተለየ ሁኔታ ለኢትዮጵያ አገራዊ እና ፕሮጀክት ሁኔታ እና ፍላጎቶች ተስማሚ እንዲሆኑ ተደርገው ነው። ይህም በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ መሪ ቤተሰቦች እና በማህበረሰባቸው ላይ የሚያስከትለውን ተጠባቂ ውጤት ለመዳሰስ በተለይ በመስኖ የሚለማ እና የማይለማ መሬት አያያዝ፣ የአልሚ ምግቦች እና የገቢ ማስገኛ እድሎች ተደራሽነት ላይ መጠይቆችን፣ መመሪያዎችን እና መሳሪያዎችን በማካተት ተዘጋጅቷል። የናሙና አወሳሰድ አካሄዱም የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራን የመስፋት እና ወደሌሎች ተዛማችነት ውጤት ለመፈተሽ ታሳቢ ያደረገ ነበር። ከሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ (GMF) መሪ ቤተሰቦች በተጨማሪ፣ በራሳቸው የታዩ ለውጦችንና ወደ ሌሎች የመስፋት ተጨባጭ ሁኔታን ለመዳሰስ የቅርብ ጓደኞቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል።

### መረጃ ማሰባሰብ

በየካቲት እና መጋቢት ወር 2023 እ.ኤ.አ. ተሳተፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም II ከተተገበረባቸው አራት ክልሎች ውስጥ በሦስቱ ማለትም በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል። የትግራይ ክልል በጥናቱ ያልተካተተው በደህንነት ስጋቶች ችግር ምክንያት ነው። የቀድሞው የደቡብ ክልል በአራት ክልሎች የተከፋፈለ ሲሆን የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከሚገኝ የፕሮግራሙ ቀበሌ ነው። በየክልሉ አንድ የጥናት መንደር በተሳተፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም II ከሚተገበርባቸው አካባቢ እና በተመሳሳይ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ አንድ የንፅፅር መንደር ተመሳሳይ ብሔር፣ ቋንቋ እና ሃይማኖታዊ ዳራ ያለው ነገር ግን ከፕሮግራሙ ትግበራ ውጪ የሚገኙ መንደሮች ተመርጠዋል። በአጠቃላይ በጥናቱ የተካተቱት ሰድስት መንደሮች ሲሆኑ በእያንዳንዱ ክልል ሁለት መንደሮች የጥናቱ አካል ሆነዋል። የጥናት መንደሮች የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ተግባራዊ የተደረገባቸው ሶስት እና ተግባራዊ ያልተደረገባቸው ሶስት መንደሮች ሲሆኑ የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ያመጣውን ለውጥ/ተጽዕኖ ለመለየት ታሳቢ ተደርገዋል። በየክልሉ የሚገኙ የመንደሮች እያንዳንዳቸው የተለያዩ የብሔር፥ የቋንቋ እና ሃይማኖታዊ መስተጋብሮችን ይወክላሉ። አራት ቋንቋዎች እና ሶስት የሃይማኖት ቡድኖች አማርኛ (ክርስቲያን ኦርቶዶክስ)፣ ኦሮሚያ (ሙስሊም)፣ እንዲሁም ካምቤቴኛ እና ሀዴኛ (ክርስቲያን ፕሮቴስታንት)ተካተዋል።



የዓለም አቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ እና የተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ሁለት ሠራተኞችን በሁሉም ደረጃ (ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ)፥ በተለይም የክትትልና ግምገማ እና የሥርዓተ ፆታና የሥርዓተ ምግብ ባለሙያዎች የተውጣጡ ዘጠኝ ቁልፍ መረጃ ሰጭ ጋር ስለ ፕሮጀክቱ፣ ማህበረሰቦች እና የሴቶች ሃብት መብት ላይ ተጽዕኖ ስላደረጉ ነገሮችና ሁኔታዎች ቃለ መጠይቅ ተደርገው መረጃ ሰጥተዋል።



ለእያንዳንዱ የተመረጡት ሰድስት ማህበረሰቦች የማህበረሰብ መገለጫዎች ተፈጥረዋል። ሁለት በወረዳ የሚሰሩ ባለሙያዎች፥ የተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ባለሙያዎች፣ የቀበሌ ልማት ሠራተኞችና የቀበሌ መሪዎች በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ቃለ መጠይቅ ሰጥተዋል።



በሁሉም የጥናቱ መንደሮች በሚገኙ ማህበረሰቦች የአትኩሮት ቡድን ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን ተሳታፊዎች በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ስልጠና የወሰዱና ያልወሰዱ ቤተሰቦችን ያካተቱ ቡድኖችን መሰረት አድርጓል። ይህም እያንዳንዳቸው ከ 4 እስከ 12 ተሳታፊዎች ያሉት 18 የአትኩሮት ቡድን ውይይቶችን አካትቷል። በጥናቱ ወቅት ጥቅም ላይ የዋለው የአትኩሮት ቡድን መመሪያ ስለማህበረሰብ አውድ፣ ስለነባር የመሬት እና ተያያዥ የሀብት መብቶች፣ ስለነዚህ መብቶች ተጠቃሚ ለመሆን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች እና ስለሚኖሩ የመፍትሄዎች ሃሳቦችን ያካተተ ነበር።



ለሥርዓተ ፆታ ትንተናው በኢትዮጵያ ተጨማሪ የዳሰሳ ጥናት መሳሪያ የተዘጋጀ ሲሆን የጥንዶች፣ የቤተሰብ/ጓደኞች ቃለ መጠይቅ ያካትታል። በዚህም መሰረት ጥንዶች (ሚስት እና ባል) በተናጠል ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሲሆን እያንዳንዳቸው በተመረጡ የቅርብ የቤተሰብ አባል ወይም ተመሳሳይ ፆታ ያለው ጓደኛ ጋር፣ የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ በጥንዶቹ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ለመረዳት፣ ከእነሱ ቅርበት አንጻር ዳሰሳ ተደርጓል። በጥናት መንደሮች ሁለት የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ መሪ ቤተሰቦች የሆኑ ጥንዶች እና ጓደኞቻቸው/ቤተሰቦቻቸው (ማለትም የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ጥንዶች)፣ እና ሌሎች ሁለት በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ስልጠና ያልወሰዱ ጥንዶችና ጓደኞቻቸው/ ቤተሰቦቻቸው (የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ያልሆኑ ጥንዶች) (8 ሴቶች + 8 ወንዶች) ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል። በጥናት መንደሮች፣ ሁለት የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ያልሆኑ ጥንዶች እና ቤተሰቦቻቸው/ጓደኞቻቸው (4 ሴቶች + 4 ወንዶች) ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል። በአጠቃላይ፣ 72 (36 ሴቶች፣ 36 ወንዶች) ቃለ መጠይቆች ተደርገዋል።.



በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳተፊ ያልሆነ የአትኩሮት ቡድን ውይይት ተሳታፊ አባዎራዎች በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል © 2023, ዶ/ር ስቲብኒቲ አትማጃ



# ከጥናቱ የተገኙ ቁልፍ ትምህርቶች



### 01

### የሁለንተናዊ ደህንነት ጽንሰ-ሀሳብ:

በሁሉም መስኮች በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያሉትን ግልጽ ልዩነቶች አሉታዊ ልማዳዊ እምነቶች እና የማህበረሰብ ግንዛቤዎች ተጽዕኖ እንዳላቸው በመገንዘብ ማረም ያስፈልጋል። በሴት የሚመሩ ቤተሰቦች (እማወራዎች) የተለያዩ ችግሮች ይገጥማቸዋል ከንዚህም ውስጥ የተገደበ እንቅስቃሴ፣ አድልዎ እና ድህነት በዋንኛንት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ልዩነቶች የቤተሰብ መካከል ግጭቶችን፣ በመሬት እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያለውን የማይመጣጠን የወንድ የበላይነት ቁጥጥርን ያካትታሉ። ይህም ያላገቡ ሴቶችን ካገቡ ሴቶች በታች እና ሁሉንም (ያገቡትንም ያላገቡትንም ሴቶች) ከወንዶች በታች የሚያስቀምጡ ልማዳዊ አመለካከቶች በመኖራቸው ነው። በሁሉም ይሄ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች በቤተሰብ ውስጥ የተሻለ ፍቅር፣ መግባባት እና ትብብር እንዳለ ያሳያል። ይህ ከሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ዓላማዎች ጋር ያለውን መጣጣም በጉልህ የሚያሳይ ሲሆን፤ የስልጠና ፍላጐት መኖር፡ ሥርዓተ ፆታ ተኮር ልማዶች እና ጎጅ አመለካከቶች ምንም ይሁኑ ምን፣ ለመለወጥ ጠንካራ ፍላጎት  መኖሩን ያሳያል።

### 02

### የሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብት:

በሁሉም የጥናት መንደሮች ሴቶች በዋናነት የመሬት ባለቤትነት መብቶችን የሚያገኙት ከወላጆች ወይም ከባሎች በውርስ እና በጋብቻ ነው። በጋብቻ እና በጋብቻ ውስጥ ካሉ የመሬት ባለቤቶች ጋር ግንኙነት ባለመኖሩ ምክንያት ከሌላ አካባቢ በተለያየ ምክንያት የሚመጡ አዲስ ነዋሪዎች የመሬት መብቶችን በማግኘት ረገድ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የእኩልነት መብትን የሚጠብቅ ቢሆንም፣ የመሬት ውርስ በሥርዓተ ፆታ ላይ በተመሰረቱ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ልማዶች የተገደበ ሲሆን በሁለት ክልሎች በሚገኙ አራት የጥናት መንደሮች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች እህት ወንድሞቻቸው ወይም ግማሽ ወይም ምንም የማይወርሱበት ሁኔታ ይስተዋላል።



### 03

### የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በመሬት አስተዳደር ተግባራት ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ:-

በኦሮሚያ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በሚገኙ የተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ፪ የሥርዓተ ፆታ ጥናቱ አካል በሆኑ መንደሮች ውስጥ በእርሻ መሬት አስተዳደር ላይ የሴቶች ተሳትፎላይ አዎንታዊ ለውጦች ታይተዋል። ይህም በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ እና በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር (IWUA) ውስጥ የሴቶች አባልነት መጨመር ምክንያት ተጠቃሽ ነው። በአማራ ክልል ደግሞ የጋራ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መብት ለእኩል የመሬት ባለቤትነት ሚና አስተዋፅዖ አድርጓል። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ካመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ውስጥ ግጭትን መቀነስ፣ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በጋራ በመከፋፈል መስራት እና ውሳኔዎች ላይ በጋራ መሳተፍ የሚጠቀሱ ዋና ዋናዎቹ ለውጦች ናቸው።

### 04

### የሴቶች በግብርና ተግባራት ላይ ያላቸው አስተዋጽዖ እውቅና ውስንነት:-

ምንም እንኳን ሴቶች ግብርና ስራ የሚያበረክቱት ጉልህ አስተዋጽኦ ቢኖርም በግብርና እና ደህንነት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ማህበረሰቡ የሚሰጠው እውቅና ውስን ነው። ከሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በኋላ የሚወሰዱ የመፍትሄዎች ሃሳቦች ብዙውን ጊዜ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለውን ትብብር የሚያሳዩ ሲሆን የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ያለውን እምቅ ድርሻ ያሳያል። ለምሳሌ ለአስቸኳይ ጊዜ የቤት እንስሳት ሽያጭ ባለቤትነት መብት የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ያተኮሩ እርምጃዎች ውስጥ ይካተታሉ።



## 05

### በሃብት ተጠቃሚነት አኳያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ሥርዓተ ፆታ ኢፍትሃዊነት ፡

በመሬትና ተያያዥ የሀብት ባለቤትነት መብቶች እኩልነት አለመኖር ምክንያት በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሴቶች ዝቅተኛ ውክልና እና ሴቶችን ደካማ አድርጎ የሚያይ አመለካከት ሰር እንደሰደደ ቀጥሏል። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ሥልጠና እነዚህን ኢፍትሃዊነቶች ለመፍታት እንደ አንድ ወሳኝ መፍትሄ ሆኖ የተወሰደ ሲሆን አማራጭ ሃሳቦች እና እርምጃዎች እንደሚያስፈልጉ ያሳያል።

## 06

### በመስኖ የሚለሙ መሬቶች ላይ ያሉ የሥርዓተ ፆታ ልማዳዊ አስተሳሰቦች፡

የመስኖ መሠረተ ልማት ባለባቸው እና መስኖ በሌላቸው አካባቢዎች መካከል ከመሬት ጋር የተያያዙ የሥርዓተ ፆታ ልማዳዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ናቸው። በኦሮሚያ የመስኖ መሠረተ ልማት መግባት የበለጠ እኩል የሥርዓተ ፆታ አስተሳሰብ እንዲኖር አድርጓል። ይህ ለውጥ በተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ሁለት በሴቶች እና በሴት የቤተሰብ ኃላፊዎች ተጠቀሚነት ላይ ባለው ትኩረት ምክንያት የተፈጠረ ወይም  በመስኖ ፕሮጀክቶች ምክንያት ስለመሆኑና ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም።

## 07

### የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በጥንዶች እና በደህንነት ላይ ያለው ተጽዕኖ፡

የጥናቱ አካል በሆኑ መንደሮች ያሉ ማህበረሰብ አባል የሆኑ ባለትዳር ጥንዶች በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ለመሳተፍ ያላቸው ተነሳሽነት እና የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ (GMF) ትግበራ ዓላማዎችን በመረዳት የተናበበ መልዕክት መኖሩን ያመለክታል። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ለጥንዶች እርስ በርስ መተባበር፣ እኩልነት እና መግባባት እንዲመጣ በአዎንታዊ መልኩ አስተዋጽኦ አድርጓል። በቤተሰቦች ውስጥ ሰላም እና ፍቅርን በማጎልበት እና በጊዜ ሂደት አዎንታዊ ለውጦችን  አምጥቷል።





የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊ በአነስተኛ መስኖ መስረተ ልማት የለማ ማሳ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ሃደሮ ጡንጦ ወረዳ ጎምቦሎዞ መስኖ ልማት ተቋም © 2023, ዶ/ር ስቲብኒቲ አትማጃ



## 08

### በሥርዓተ ፆታ ተኮር ልማዳዊ ህጎች እና ኃላፊነቶች ላይ የሚታየው ለውጥ፡

በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊዎች እና ተሳታፊ ካልሆኑት ጋር ሲነጻጸር በቤተሰብ ደረጃ የሥራ ክፍፍል እና ኃላፊነቶችን በተመለከተ የበለጠ ፍትሃዊ አመለካከት አጎልብተዋል። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በጥንዶች እና በቤተሰቦቻቸው/ጓደኞቻቸው መካከል በማህበራዊ ህጎችና ልማዶች ላይ ለውጥን የሚያመጣ ቢሆንም፣ ይህንን ተጽዕኖ ወደ ሰፊው ማህበረሰብ ለማስፋፋት በማህበረሰብ ደረጃ የሥርዓተ ፆታ ሚናዎችን እና ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ ተጨማሪ ስልቶች ሊያስፈልጉ ይችላሉ። የሚታዩ ለውጦች ቢኖሩም በማህበረሰብ ደረጃ ጠቃሚ ኃላፊነቶችን ለሴቶች ከመመስጠት አኳያ አሁንም የሚታዩ ክፍተቶች አሉ። ይህም ከቤተሰብ/ጓደኞች ተጽዕኖ  አልፎ ተርፎ ተግባራዊ ጥረቶች እንደሚያስፈልጉ ያሳያል።

## 09

### በፍትሃዊ ሥራ ክፍፍል ላይ ያመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ፡

የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በጥንዶች መካከል በሥራ ክፍፍል ላይ አዎታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። ፍትሃዊ የቤት ውስጥ ሥራን ለመከፋፈል፣ የገቢ እድሎችን፣ ውሳኔ አሰጣጥን እና ጊዜን በበውጤታማነት መጠቀምን ሙሉ ፈቃደኝነት አጎልብቷል። እንደ ወንዶች ከወግና ከልማድ አኳያ የሚመጣውን ተቃውሞ የመፍራት ስጋቶች ቢኖሩም፣ በቅርብ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ከታዩ ተጨባጭ ለውጦች ዋና ዋናዎቹ ግጭትን የመቀነስ፣ ገቢን የመጨመር እና የተሻለ ደህንነት ማረጋገጥን ጨምሮ በፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ የሥራ ክፍፍልን በተመለከተ በአመለካከት ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል።

## 10

### በግልጽ የሚታይ የባህል፥ ወግና ልማድ ለውጥ

የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ በማህበራዊ ወጎች ላይ ያለው አዎንታዊ ተጽዕኖ በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ጥንዶች እና በዙሪያቸው ያሉ ጓደኞቻቸውና ወገኖቻቸው ዘንድ በግልጽ የሚጸባረቅ ሲሆን በባህላዊ መንገድ በወንዶች የበላይነት ተይዘው የነበሩ ተግባራት የሴቶችን የመሳተፍ እድላቸው ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳያል። ይሁን እንጂ፣ ይህ ጅምር ለውጥ ገና ወደ ሰፊው ማህበረሰብ አልተስፋፋም፣ ይህም የሥርዓተ ፆታ እኩልነትመርሆዎችን ተቀባይነት ለማሰፋት ቀጣይነት ያለው ጥረት እንደሚያስፈልግ ያሳያል።

## ዋቢ መረጃዎች





ለምግብ ዋስትና፣ ለተሻሻለ አመጋገብ እና ለዘላቂ ግብርና የሥርዓተ-ፆታ ሽግግር ዘዴዎች የመልካም ተሞክሮዎች ስብሰብ (https://doi.org/10.4060/cb1331en) በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ጋር በመተባበር ተዘጋጀ።

## ምስጋና

ይህ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና የተካሄደው በሚከተሉት ግለሰቦች እና ተቋማት የቅርብ ትብብር ነው። አቶ ኑረዲን አሳሮ፣ ያረጋል ዘላለም  (ከተሳትፏዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ሁለት የግብርና  ሚኒስቴር)፣ ሃይ ሃ ቩቲ እና ሉሲ ቬርጋሪ (ከዓለም አቀፍ  የግብርና ልማት ፈንድ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት)፣ ተሾመ በየነ፣ ቤርሳቤህ  ሃይሉ፣ ነፃነት አለማየሁ፣ የእብሰራ ታምራት፣ ማህሌት ነጋሳ እና ዳግም ዮሴፍ (የመሰክ ጥናት ቡድን አባላት CIFOR-ICRAF  ኢትዮጵያ) እና ዶ/ር ስቲብኒቲ አትማጃ (የጥናቱ መሪ፣ CIFOR-ICRAF)

# ምክረ-ሃሳቦች

የመሬትና ተያያዥ የሃብት መብቶችን ተጠቃሚነትን ለማጠናከር እና የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እንዲሁም የሚከናኑ ተግባራት ውጤታማነትን ለማሳደግ የተለያዩ ምክረ ሃሳቦች ቀርበዋል።

01

**የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራን ከፕሮግራም አጀማመር ጋር ያስተሳስሩ፡**
በፕሮግራሙ ዲዛይን መጀመሪያ ላይ የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ መርሆዎችን እና ልምዶችን ታሳቢ በማድረግ የፕሮግራም-አቀፋዊ ጥቅምን ለማሳደግ የቤት ውስጥ መረዳዳትን፣ የእውቀት ቅብብሎሽ፣ ፍትሃዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የቤት ውስጥ ጉልበት ውጤታማነት ማሳደግ ያስፈልጋል።

02

**ክትትል እና ግምገማን አሰራርን ያሻሽሉ፡**
የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራን ዓይነታዊ እና መጠናዊ የመረጃ ማሰባሰብን በሚያጎለብት አካታች የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል። ብዙውን ጊዜ በተለምዶ በቤተሰብ ደረጃ እንዲሁም በቅርብ ቤተሰብ፣ በማህበረሰብ ደረጃ ያሉ ተዛማጅነት ያላቸው ለውጦችን ለመያዝ ትኩረት ከማይሰጣቸው አመልካቾች ባሻገር ሌሎች ቀጥተኛ የሆኑ ውጤቶችን መያዝ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ተገቢ ነው።

03

**የአዋጭነት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፡**
የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ አተገባበር ከሌሎች ተግባራት ጋር ሲነጻጸር የሀብት ድልድልን ለመረዳትና በጀቱን በመለየት ለገንዘብ የሚሰጠውን ዋጋ ይገምግሙ። በተለያዩ ደረጃዎች (ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ማህበረሰቦች) ያሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ተዛማች ውጤቶችን በመመርመር ወጪን የሚቆጥቡ መንገዶች ይለዩ።



04

**የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራን በማህበረሰብ ደረጃ ካሉ ስልቶች ጋር ያጣምሩ፡**
የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራን ከሌሎች ተጨማሪ የማህበረሰብ አቀፍ የሥርዓተ ፆታ ወጎችና ልማዶች ከሚለውጡ ዘዴዎች ጋር በማዋሃድ/ በማጣመር በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦችን እና የእማዋራዎችን ተደራሽነት ያረጋግጡ። ይህ ጥምረት ከሥርዓተ ፆታ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ፈታኝ ጉደዮችን መፍታት ይችላል።

05

**ክትትልና ግምገማ ስርዓት ውስጥ አዎንታዊ/ለስላሳ አመልካቾችን ያካትቱ፡**
የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ውጤታማነትን ለመለካት በክትትልና ግምገማ ማዕቀፎች ውስጥ እንደ ፍቅር፣ ክብር፣ ጥቃት/ግጭትን መቀነስ፣ የምግብ ዋስትና እና የገቢ መረጋጋት የመሳሰሉ አዎንታዊ /"ለስላሳ"/ አመልካች መለኪያዎችን ያካትቱ። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተጽዕኖዎችን መረጃ ለመያዝ ከሙያዊ አመልካቾች ባሻገር የበለጠ ሌሎችንም ይጠቀሙ።

06

**ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ውጤቶችን ይገምግሙ፡**
በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ውጤቶችን ታሳቢ ያደረጉ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፎችን ይቀርጹ። ቀጥተኛ ውጤቶች በቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን መቀነስ እና መከባበርንና መተሳሰብን ያካትታሉ፣ ቀጥተኛ ያልሆኑ ውጤቶች ደግሞ የእናቶችንና እና የህጻናትን ጤና ማሻሻል፣ የቤተሰብን ጥሪት ማሳደግ እና የኑሮ ሁኔታን እና የምግብ ዋስትናን ማሻሻልን ያካትታሉ።

07

**የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ የሥልጠና ጊዜ ሥራ አመራርን ያሳድጉ፡**
በመጀመሪያው ወሳኙ አንድ ዓመት የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊዎች የሚያገጥሟቸውን ተግዳሮቶች በመለየት እና ሌሎችን ለማስተማር ያላቸውንም ሚና በመረዳት እውቅና መስጠት እና ከፍተኛ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊዎች ዘንድ ያለውን ለውጥ ለማስቀጠልና ወደኋላ እንዳይመለስ የአመቻች ሰራተኞች ፍልሰትን ጨምሮ በህብተሰቡ ዘንድ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን መፍታት ያስፈልጋል።

08

**ከልማት አጀንዳዎች ጋር ያሉ ቅንጅታዊ አሰራሮችን ያሰሉ፡**
የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ከልማት አጀንዳ ጋር ያለውን ትስስር በመጠቀም በብሔራዊ እና በማህበረሰብ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት እንዲኖረው ያድርጉ። የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተጽዕኖን ለማሳደግ በተጽዕኖ ፈጣሪ ወኪሎች ውስጥ ያሉ ፕሮግራሞችን እና መዋቅሮችን ይጠቀሙ።

09

**ፕሮጀክቱ ትግበራ አካላት ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ፍትሃዊነትን ያጠናክሩ፡** በፕሮግራሙ ትግበራ አካላት ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ምጥጥን እንዲኖር ጥረት ያድርጉ፣ በፕሮግራሙ የሥርዓተ ፆታ ሽግግር ዘዴ ዓላማዎችን ለማሳካትና ያላቸውን ጠቀሜታ በተመለከተ የቡድን ጥምርታ ተጽዕኖንና በማህበረሰቡና በቡድን አጋሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያለውን ተጽዕኖ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል። በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ተሳታፊዎች ምልመላ ላይ ፈታኝ ሁኔታዎች ሊኖሩ ቢችሉም፣ ወንድ የማህበረሰብ መሪዎችን እና የቤተሰብ ኃላፊዎችን የሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ GMF ትግበራን እንዲቀበሉ ለማሳመን የሥርዓተ ፆታ ቅይጥ ቡድኖች ያላቸውን አዎንታዊ ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ

10

**ማህበረሰብ ተኮር ድጋፍንና የጋራ መማርን ማበረታት፡**
በሥርዓተ ፆታ ሞዴል ቤተሰብ ትግበራ ሰልጣኞች መካከል ያለውን ማህበረሰብ ተኮር ድጋፍ እና የጋራ መማር ጠቀሜታ ያሳድጉ። ሰልጣኞች እና ሌሎች ቤተሰቦች የጋራ ድጋፍ ለመስጠት፣ ልምዶችን ለመለዋወጥ፣ ምክር ለመጠየቅ እና ተነሳሽነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ወርሃዊ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ድጋፍ ሰጪ መርሃግብር ይፍጠሩ።



## የፕሮጀክቱ ትግበራ ጥምረት

የአለም አቀፉ የደን ምርምር ማዕከል (CIFOR) እና የአለም ጥምር ግብርና (ICRAF) በሁሉም መልክዓ ምድሮች፣ ከደረቅ መሬት እስከ እርጥበት አዘል አካባቢዎች ያሉ ዛፎች አካባቢን እና የሁሉንም ሰው ደህንነት የሚያሻሽሉበትን የበለጠ ፍትሃዊ የሆነ ዓለም ይመኛሉ። CIFOR እና ICRAF የCGIAR የምርምር ማዕከላት አካላት ናቸው።.

የአየር ንብረት ለውጥ፣ የብዝሃ ሕይወት መመናመን፣ የአካባቢ መራቆት እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት። እነዚህ አራት ተያያዝነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ቀውሶች ለብዙ ዓመታት የዓለማችንን የኑሮ መተዳደሪያን ደህንነት አደጋ ላይ ጥለውታል። በኮቪድ-19 ምክንያት በግብርና፣ በመሬት አጠቃቀም፣ በብዝሀ ሕይወት እና በሰዎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ያለው ተጽእኖ አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ አስቸጋሪ ሆኗል። ይህንን አሉታዊ አዝማሚያ መቀልበስ ፈታኝ ነው። ነገር ግን ቅንጅታዊ አሰራርን በድፍረት መምረጥ መፍትሄዎችን ለማምጣት መልካም አጋጣሚ ነው። እ.ኤ.አ. በ 2019 የተቋቋመው የባዮቨርሲቲ ዓለም አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የትሮፒካል ግብርና ማዕከል (ሲአይኤቲ) የተቋቋሙት እነዚህን አራት ቀውሶች ለመቅረፍ ነው፣ ይህም በምግብ ስርዓቱ ውስጥ ባሉ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያለው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።

የዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ኢንስቲትዩት (IFPRI) በማደግ ላይ ባሉ አገራት ውስጥ ድህነትን በዘላቂነት ለመቀነስ እና ረሃብንና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለማስቆም በምርምር ላይ የተመሰረተ የፖሊሲ መፍትሄዎችን ይሰጣል። በ1975 የተቋቋመው IFPRI አሁን ከ50 በላይ በሆኑ አገራት ውስጥ ከ600 በላይ ሰራተኞች አሉት። ይህ ተቋም በልማት ዙሪያ የግብርና ምርምር በሚያካሂደው የCGIAR የዓለም አቀፍ ሽርክና የምርምር ማዕከል ነው።

## የፕሮግራሙ ተጠሪዎች


**አን ኤም. ላርሰን፣**
**የአስተዳደር፣ ፍትህ እና ደህንነት ቡድን መሪ**
a.larson@cifor-icraf.org

**ማርሌን ኤልያስ፣**
**የሰርዓተ ፆታ ማካተት ዳይሬክተር**
marlene.elias@cgiar.org

**ቲሽሪንግ ቾደን፡**
**በሥርዓተ-ፆታ ቡድን የሥርዓተ-ፆታ እና ማህበራዊ ማካተት ቴክኒካል ባለሙያ**
t.choden@ifad.org

**ሪኬ ግራንድ ኦሊቬራ፡**
**የመሬት ስሪት ቡድን መሪ የቴክኒክ ባለሙያ**
r.olivera@ifad.org



ይህ ሰነድ የተዘጋጀው በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ (IFAD) የገንዘብ ድጋፍ ነው። በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት ግኝቶች፣ አስተያየቶች፣ ትርጓሜዎች እና መደምደሚያዎች የጸሐፊዎቹ እንጂ የግድ የኢፋድን፣ የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ፣ የአባላቱን ወይም የሚወክሉትን አባል ሀገራትን አመለካከት የሚያንፀባርቁ አይደሉም። አለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ በዚህ ሥራ ውስጥ የተካተቱትን መረጃዎች ትክክለኛነት አያረጋግጥም። በዚህ ስራ ውስጥ በማንኛው ካርታ ላይ የሚታዩት ድንበሮች፣ ቀለሞች፣ ስያሜዎች እና ሌሎች መረጃዎን ሕጋዊነት ወይም እንደዚህ ያሉ ድንበሮችን ማጽደቅና ተቀባይነት መስጠት የሚያሳዩ ምንም ዓይነት ውሳኔ ዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድን አይመለከትም።


https://www.cifor-icraf.org/wlr
https://www.ifad.org/en/gender_transformative_approaches

